# ተሰፍቶ በልኩ

አለ እዚያ ማዶ ፣ አጉል የሚፎክር
ዛሬም በስተርጅና ፣ ፀጉሩን ሊያጎፍር
የመቀበሪያውን ፣ ጉድጓድ የሚቆፍር
ንሰሃውን ገብቶ ፣ ቀኑን እንዳይቆጥር
ከዘራውን ይዞ ፣ ይላል እምቡር እምቡር ።

ፊቱ ተጨማዶ ፣ ፀጉሩ ሸብቶ
ዲያፐር አጥልቆ ፣ ግልገል ሱሪው ቀርቶ
ስኳር ደም ብዛቱ ፣ ሽቅብ ጣሪያ ነክቶ
ያዛውንቶች መንጋ ፣ ሽምድምድ እንኩቶ
ጫካ ሊገባ ነው ፣ ኢንሱን አንግቶ ።

በመዝረፍ በመግደል ፣ በደም የሰከረው
አንድ እርከን ለመውጣት ፣ ትንፋሽ እያጠረው
በምናብ የሚኖር ፣ ትዕቢት የወጠረው
አፈር ትቢያ ሊሆን ፣ አንድ ሃሙስ የቀረው
አቅሙን ዘንግቶት ፣ ጠፍቶ የሚመከረው
ሰፋጣ ያበዛል ፣ ሞቱን ላያስቀረው
ከንቱ መንፈራገጥ ፣ አወይ የቸገረው ።

ከራሱ የተጣላ ፣ ምድረ ሽማግሌ
እነሱ በበሉት ፣ በላሱት አሞሌ
ተጋሩን እንዳለ ፣ አድርገውት ጀሌ
ደሙን ሊጎነጩ ፣ ቀድተው በብርሌ
የጦር ያለህ ይላል ፣ ያዛውንት ባተሌ ።

በስተርጅና ዘመን ፣ በወጉ እንዳይሞቱ
በንሰሃ ዘመን ፣ እንዲያው ያላባቱ
ጦር አምጣ ልመና ፣ ነጋሪት መምታቱ
የውሻ ሞት ልሙት ፣ ይላል አዛውንቱ
የመረጠው ይሁን ፣ ይሰማ ፀሎቱ ።

ሚዛን የማይደፉ ፣ ቢሰፈር ቢለኩ
ጥፋትና ውድመት ፣ የሆነ ታሪኩ
ወሮበላ ገዝተው ፣ አገር የሚያውኩ
አልሞትንም ለማለት ፣ ሸሽተው የሚያስካኩ
ቁምጣው ካልተሰጠው ፣ ተሰፍቶ በልኩ
አልታይ ብሎታል ፣ ሽንፈት መንበርከኩ ።

ታዛቢው

January 7, 2019